የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፪ሺ፲፬

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No 17
ADDIS ABABA 29th March, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፭/፪ሺ፲፬
ጣና በለስ ስኳር ፋብሪካን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……..ገጽ ፲፬ሺ፺፮

## ደንብ ቁጥር ፬፻፺፭/፪ሺ፲፬

**ጣና በለስ ስኳር ፋብሪካን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “ጣና በለስ ስኳር ፋብሪካን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፭/፪ሺ፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ ጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ ከዚህ በኋላ “ፋብሪካ” እየተባለ የሚጠራው የፌደራል የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪/ ጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

## Content

Regulation No. 495/2022
Council of Ministers Regulation to Provide for The Establishment of Tana Beles Sugar Factory……..............................................Page 14096

## REGULATION NO. 495/2022

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF TANA BELES SUGAR FACTORY**

This regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as "Tana Beles Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 495/2022”.

**2. Establishment**

1/ Tana Beles Sugar Factory, hereinafter referred to as “The Factory” is hereby established as a Federal Public Enterprise;

2/ Tana Beles Sugar Factory shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

፫. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ ፭፻፶ መሠረት የፋብሪካውን የንግድ ስራ ጉዳዮች የመምራት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የፋብሪካው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ ዋና መሥሪያ ቤት ጃዊ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌላ ሥፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

ፋብሪካው የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ተክሎችን ማልማት፤

፪/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶች እና ተጓዳኝ ምርቶችን ማምረት፤

፫/ ስኳር፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችንና ተጓዳኝ ምርቶችን በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በኩል ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

፬/ የፋብሪካውን የስኳር ልማት ማስፋፊያ መልሶ የማደስ ፕሮጀክቶችን ማቀድና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፭/ በአዋጪነትና በውጤታማነት ላይ ተመስርቶ እንደ አስፈላጊነቱ ከአገዳ አብቃዮች ጋር ውል ገብቶ መስራት፤

፮/ ለፋብሪካው የሚያስፈልገውን የሠለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት መስራት፤

3. **Supervisory Authority**

Without prejudice to the right of the Ethiopian Sugar Industry Group Pursuant to Article 550 of the Ethiopian Commercial Code to direct the business affairs of the factory, the Public Enterprises Holding and Administration shall be the Supervisory Authority of the Factory.

4. **Head Office**

The Head Office of Tana Beles Sugar Factory shall be in Jawi town and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. **Purpose**

The purposes for which the Factory is established are:

1/ To grow sugar cane and other sugar yielding plants;

2/ To process and produce sugar, sugar by-products and co-products;

3/ To supply sugar and sugar by products and co-products to local as well as foreign market through the Ethiopian Sugar Industry Group;

4/ To plan sugar development expansion and overhaul projects within the factory and implement same upon approval;

5/ To work in agreement with sugar cane growers based on feasibility and effectiveness;

6/ Work to produce the required trained manpower in number, type and quality;

፯/ ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የሸንኮራ አገዳ እርሻ መሬት በሊዝ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ ማግኘትና በይዞታው ሥር ማድረግና ማልማት፤

፰/ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚሰጠውን የፖሊሲ አቅጣጫና የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል ተደራድሮ በመፈረም ገንዘብ መበደር፤

፱/ የፋብሪካውን የማምረት አቅም የሚጨምሩ አዲስ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትን ሥልጠናንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ከሌሎች ኩባንያዎች ጋር መደራደርና ውል መፈረም፤

፲/ በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ከሚከናወኑት በጋራ ማዕቀፍ ከሚገዙት ግዢዎች ውጪ ያሉትን የግዢ ውሎች በመዋዋል ግዢ መፈጸም፤

፲፩/ ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ሥራዎችን መሥራት፡፡

## ፮. ካፒታል

ለጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩፻፲ ቢሊዮን ፪፻፸፮ ሚሊዮን ፮፻፺፪ ሺ ፮፻፵፪ ብር ከ ፵፬ ሳንቲም (አንድ መቶ አስር ቢሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ስድስት መቶ አርባ ሁለት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፳፯ ቢሊዮን ፭፻፷፱ ሚሊዮን ፩፻፸፫ ሺህ ፩፻፷ ብር ከ ፷፩ ሳንቲም (ሃያ ሰባት ቢሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሶስት ሺ አንድ መቶ ስልሳ ብር ከሥልሳ አንድ ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

## ፯. ኃላፊነት

ፋብሪካው ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

7/ Acquire use right on lease or by other legal means and develop agricultural land for sugar cane plantation;

8/ In accordance with the policy direction and Directives issued by the Ministry of Finance, negotiate and sign loans with domestic as well as foreign financial institutions;

9/ Enter into a contract with other companies for introducing new technologies or training and other matters of importance that improve the factory's productivity;

10/ Execute procurements those are not included in the common procurement package that is carried out by The Ethiopian Sugar Industry Group;

11/ Engage in any other activity that is necessary to accomplish its purposes.

## 6. Capital

The authorized capital of Tana Beles Sugar Factory is Birr 110,276,692,642.44 (One Hundred Ten Billion Two Hundred Seventy Six Million Six Hundred Ninety Two Thousand Six Hundred Fourty Two Birr and Forty Four Cents) of which Birr 27,569,173,160.61 (Twenty Seven Billion Five Hundred Sixty Nine Million One Hundred Seventy Three Thousand One Hundred Sixty Birr and Sixty One Cents )is paid up in cash and in kind.

## 7. Liability

The Factory shall not be held liable beyond its total assets.

፰. **<u>የቆይታ ጊዜ</u>**

ጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

፱. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

8. **<u>Duration</u>**

Tana Beles Sugar Factory is established for an indefinite duration.

9. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 29th Day of March, 2022**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**